# መመሪያ ቁጥር 1052/2017

# የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ሰኔ፣ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1052/2017

የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተገማችነት ያለው እንዲሆን የአንድን ዕቃ፣ንብረት፣አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ ከዋጋ አገማመት ጠቅላላ መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ለመወሰን የሚያስችል ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መከፈል ያለበትን ታክስ ለማስከፈል የዕቃ፣ የንብረትና የአገልግሎት ወይም የጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ ትክክለኛ የታክስ ውሳኔ መወሰን በማስፈለጉ፣

ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በሁሉም የሚኒስቴሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የታክስ ባለሥልጣኑ የስራ ክፍሎች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና የገበያ ዋጋ መረጃ አስተዳደር ባለሙያዎች ከገበያ ዋጋ መረጃ ጋር በተያያዘ የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወሰን በማስፈለጉ፣ እና

ትክክለኛና ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃን ለታክስ ውሳኔ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 3(6) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1052/2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ትክክለኛ የገበያ ዋጋ"** ማለት የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ ነው፤

2) **"መረጃ"** ማለት የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለመወሰን የሚሰበሰብ መረጃ ነው፤

3) **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ለመሸጥ ወይም ለመግዛት በድረ ገጽ ወይም በሌሎች መንገዶች በማስተዋወቅ ግዥና ሽያጭ የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ነው፤

4) **"ልዩ ሙያ"** ማለት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለመለየት በሚደረግ ሂደት በሚኒስቴሩ ሰራተኞች ሊሸፈን የማይችል የሙያ አይነት ነው፤

5) **"መካከለኛ ዋጋ" ማለት** ተመሳሳይ ከሚገኝላቸው ከተሰበሰቡት የዋጋ ናሙናዎች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በማስቀመጥ የሚገኙት ዋጋዎች ለሙሉ ቁጥር ናሙናዎች መካከል ላይ ያሉትን ሁለቱን ናሙናዎች በመደመር ለሁለት በማካፈል የሚገኘው ዋጋ ሆኖ ለጎዶሎ ቁጥር ናሙናዎች መሀል ላይ ያለው ዋጋ ነው፤

6) **"የገበያ ሰንሰለት"** ማለት በንግድ ስራ የተሠማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ባላቸው የንግድ ግንኙነት ቅደም ተከተል መሰረት የአንድ ዕቃ ዋጋ በአምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ እና ቸርቻሪ ደረጃ ሊለያይ የሚችልበት የግብይት ሁኔታ ነው፤

7) **"ዋጋን ማጥናት"** ማለት በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን የሚደረግ ጥናት ነው፤

8) **"የገበያ ቦታ"** ማለት ግዥና ሽያጭ የሚከናወንበት ማንኛውም ቦታ ሆኖ አገልግሎትን በተመለከተ አገልግሎቱ የተሰጠበት ቦታ ማለት ነው፡፡

9) **"ማነጻጸር"** ማለት ለምርመራ የቀረበን ሰነድ በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ያላቸውን የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ከተሰበሰበ ወይም ከተከማቸ የገበያ ዋጋ መረጃ ቋትን በመጠቀም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚለይበት አሰራር ነው፤

10) **"አንድ አይነት"** ማለት በሁሉም ነገር አንድ አይነት የሆነ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ነው፤

11) **"ተመሳሳይ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም"** ማለት ከሌላው ዕቃ፣ንብረት፣አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር በባህሪ፣በጥራት በብዛት፣ በቦታ፣ በሚሰጠው አገልግሎት በሚይዛቸው ቁሶች እና በመልካም ስም ተመሳሳይ ወይም በሚቀራረብ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆነ ነው፤

12) **"የገበያ ዋጋ መረጃ ቋት"** ማለት የተሰበሰበ የገበያ ዋጋ መረጃ ተተንትኖ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚሆንበት የቴክኖሎጂ ሥርዓት ነው፤

13) **"የገበያ ዋጋ መረጃ ተጠቃሚ"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የታክስ ውሳኔ የሚሰጥ ማንኛውም አካል ነው፤

14) **"ተባባሪ"** ማለት ማንኛውም የገበያ ዋጋ መረጃ የሚሰጥ ሰው ነው፡፡

15) **"አቅራቢ"** ማለት የገበያ ዋጋ መረጃ ከየገበያ ቦታዎች በጊዜ፣በዕቃ ወይም በአገልግሎት አይነት አደራጅቶ ለታክስ ባለሥልጣኑ የሚሸጥ ሰው ነው፤

16) **"ታማኝ ግብር ከፋይ"** ማለት በግብር ዘመኑ በንግድ እንቅስቃሴያቸው እና በታክስ ሥርዓቱ ላበረከቱት የተሻለ አፈጻጸም በተቋሙ ተለይተው እውቅና እና ሽልማት የተሰጠው ግብር ከፋይ ነው፡፡

17) **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንም ይጨምራል፤

18) **"ሚኒስቴር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ነው፤

19) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ተፈጻሚነት አለው፤

21) በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሃረጎች በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ እና በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

### 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በታክስ ህግ መሠረት የታክስ ውሳኔ ለመወሰን ሲባል የአንድን ዕቃ፣ንብረት፣አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋን ለመለየት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ እና ትንተና</u>

### 4. <u>የገበያ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚደራጅበት ሁኔታ</u>

1) የታክስ ባለሥልጣኑ የሥራ ክፍሎች ለታክስ አወሳሰን ሲባል የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም በተመለከተ የወቅቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ ተጠንቶ እንዲሰጣቸው ለታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የስራ ክፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ በቀረበው ጥያቄ መሰረት የገበያ ዋጋ መረጃ ተሰብስበው ለጥቅም ዝግጁ ያደርጋል፤

2) የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የስራ ክፍል ከታክስ ባለሥልጣኑ የስራ ክፍሎች የፍላጎት ዳሰሳ በማድረግና መሰብሰብ አለባቸው ብሎ ከሚለያቸው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ በመሰብሰብ ያደራጃል፡፡

3) የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የስራ ክፍል ከስጋትና ህግ ተገዥነት ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት፣ ከታክስ ማጭበርበርና ምርመራ ዳይሬክቶሬት፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በታክስ ባለሥልጣኑ ስር ካሉት ሌሎች የስራ ክፍሎች ስጋት የሆኑና በገቢ አሰባሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጡትን የንግድ ዘርፎችን በመለየት የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ዋጋቸውን በመለየት ያደረጃል፡፡

## 5. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ ምንጮች

የገበያ ዋጋ መረጃ በአካል፣ በስልክ፣ በደብዳቤ፣ ወይም በኢሜል ወይም በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዘዴዎች፡-

1) የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግብይት ከሚደረግባቸው የገበያ ቦታዎች፤
2) ከሶስተኛ ወገን ድረ-ገፅ፤
3) ከመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ከመንግስት የልማት ድርጅት፣ ከኩባንያዎች፣
4) ከተባባሪዎች፤
5) ከአቅራቢዎች፤
6) ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ምንጮች፤

ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

## 6. ከሶስተኛ ወገን ድረ-ገፅ ከሚገኘው የገበያ ዋጋ መረጃ መሰብሰብ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) መሠረት ከድረ-ገጽ የሚሰበሰበው የገበያ ዋጋ መረጃ የዕቃ፣ንብረት፣አገልግሎት ወይም ጥቅም ግብይት ለማከናወን በድረ-ገጽ ላይ የሚገለጹ ዋጋዎች ሲሆን ትክክለኛነቱ በሌሎች የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች መሠረት በማረጋገጥ ለጥቅም ዝግጁ ይደረጋል፡፡

## 7. ከመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ከመንግስት ልማት ድርጅቶች እና ኩባንያዎች የሚገኘው የገበያ ዋጋ መረጃ

የሚፈለገው የገበያ ዋጋ መረጃ ከኢትዮጵያ ስታቲስትክስ አገልግሎት፣ ከንግድና ቀጠናዎች ትስስር ሚኒስቴር፣ ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ከብሄራዊ ባንክ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከመንግስት ግዥ አገልግሎት፣ ከመንግስት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን፣ ከኢትዮጲያ ምርት ገበያ ድርጅት፣ ከንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ከካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ ከኢትዮጵያ የሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ከአክሲዮን ድርጅቶች እና ከሌሎች የመንግስት እና የግል ተቋማት የገበያ ዋጋ መረጃ ተሰብስቦ እንደ ገበያ ዋጋ መረጃ እንዲያገለግል ይደረጋል፡፡

## 8. ከተባባሪዎች የሚሰበሰብ የገበያ ዋጋ መረጃ

1) የታክስ ባለሥልጣኑ በየዘመኑ ታማኝ ግብር ከፋዮች ተብሎ የሚለዩ ተባባሪዎች የዋጋ መረጃ ለሚሰበስበው የስራ ክፍል መረጃውን እንዲሰጡ ይደረጋል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ የስራ ክፍል የገበያ ዋጋ መረጃ ከሚሰጥ ማንኛውም ሰው የገበያ ዋጋ መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩ ሊያደርግ ይችላል፤

3) ከተባባሪዎች የተገኘው የገበያ ዋጋ መረጃ ስለ ትክክለኛነቱ በገበያ ዋጋ መረጃ ባለሙያ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 9. ከአቅራቢዎች የሚወሰድ የገበያ ዋጋ መረጃ

1) የገበያ ዋጋ መረጃ አቅራቢዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚፈልገው መልክ መረጃውን ሲያቀርቡ እና የቀረበው መረጃ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ለጥቅም ዝግጁ የሚደረግ ይሆናል፤
2) የገበያ ዋጋ መረጃ የሚሰበስብና የሚያደራጅ የስራ ክፍል በአቅራቢዎች መቅረብ ያለበትን የገበያ ዋጋ መረጃ በአቅራቢዎች እንዲቀርብ በታክስ ባለሥልጣኑ የታክስ ሥርዓት ዘርፍ ኃላፊ ሲወሰን የገበያ ዋጋ መረጃ የሚያቀርብ አቅራቢ በመንግስት የግዥ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ተለይቶ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

## 10. የገበያ ዋጋ መረጃ ትንተና ዘዴዎች

የሚከተሉት የገበያ ዋጋ መረጃ ትንተና ዘዴዎች ናቸው፡-

1) በገበያ ቦታ የገበያ ዋጋ መረጃ ትንተና ዘዴ፤
2) በጊዜ የገበያ ዋጋ መረጃ ትንተና ዘዴ፡፡
3) የንጽጽር ዘዴ

## 11. በገበያ ቦታ የገበያ ዋጋ ትንተና ዘዴ

1) አንድ አይነት ዕቃ፣ ንብረት ወይም አገልግሎት ከአንድ የገበያ ቦታ የተሰበሰበ የገበያ ዋጋ መረጃ በተሰበሰበበት የገበያ ቦታ ትክክለኛ ዋጋ ሆኖ ያገለግላል፤
2) ተመሳሳይ የሚገኝላቸውን የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ በየገበያ ቦታዎች በገበያ ሰንሰለት አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ ሻጭና ቸርቻሪ ጋር ያሉትን ዋጋ ቢያንስ ከሶስት እስከ አምስት ናሙናዎችን በመሰብሰብ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በቅደም ተከተል በማስቀመጥ መካከል ላይ ያለውን ዋጋ የቦታው ዋጋ አድርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፤
3) በአንድ የገበያ ቦታ የናሙና ብዛት ከአራት እስከ ስድስት ማግኘት ካልተቻለ በቀረበው ናሙና ከሚቀራረብ አካባቢ የሚገኝን ናሙና በመውሰድ የገበያው ቦታ ዋጋ ለማውጣት እንደ አማራጭ ጥቅም ላይ ይውላል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ዋጋ ለማውጣት የሚያስፈልገው የናሙና ብዛት ከሚቀራረብ አከባቢ ጭምር ያልተገኘ እንደሆነ ከገበያ ቦታው የተገኘው የዋጋ መረጃ ለገበያ ቦታው በቂ ሆኖ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## 12. <u>በጊዜ የገበያ ዋጋ ትንተና ዘዴ</u>

1) የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ የስራ ክፍል ከተመረጡ ዘርፎች የአንድ እቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም የገበያ ዋጋ ቢያንስ በየወሩ ሰብስቦ በማደራጀት ለጥቅም ዝግጁ ይሆናል፤

2) የአንድ እቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም በአንድ የገበያ ቦታ በወር ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ተሰብስቦና ተተንትኖ የተዘጋጀ ዋጋ ለወሩ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

3) የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ለታክስ አወሳሰን አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የወቅቱ የገበያ ዋጋ በገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ያልተገኘ እንደሆነ ከወቅቱ በፊት ወይም በኋላ በመረጃ ቋት ውስጥ የነበረው የገበያ ዋጋ መረጃ ተወስዶ ከዋጋ ግሽበት አንጻር ወይም እንደ ሀገር ዋጋ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ያደረጉ ጉዳዮች ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የዋጋ ማስተካከያ ይሠራል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማግኘት የማይቻል ከሆነ በተቋሙ ታማኝ ግብር ከፋዮች የሆኑ ሰዎች በተባለው ጊዜ ውስጥ ሲገበያዩበት የነበረው ዋጋ ተወስዶ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይለያል፡፡

## 13. <u>የንጽጽር ዘዴ</u>

የአንድን አይነት እቃ፣ ንብረቱና አገልግሎቱ ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማግኘት የማይቻል ከሆነ የገበያ ዋጋ ማነፃፀሪያ ተደርጎ የሚወሰደው የንግድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ ለመለየት በባህሪ፣ በይዘት፣ ጥራት፣ መጠን፣ በሚሰጠው ጥቅም፣ በተፈላጊነት ደረጃ፣ በምርት ዘመንና ቦታ፣ በሻጭ ባህሪ (አምራች፣አስመጪ፣ ጅምላ ሻጭ፣ ቸርቻሪ፣ ወዘተ)፣ ሽያጩ በሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ካለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ ጋር በማነፃፀር የሚገኘው ዋጋ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

# <u>የገበያ ዋጋ መረጃ ስሌትና አጠቃቀም</u>

## 14. <u>የገበያ ዋጋ መረጃ የሚሰላበት ቀመር</u>

1) የተሰበሰበው የአንድ ዕቃ፣ ንብረትና አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ ናሙና ሳይንሳዊ በሆነ የሂሳብ ቀመር እንዲሰላ ይደረጋል፣

2) የተሰበሰበውን የአንድ ዕቃ፣ ንብረትና አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የዋጋ መረጃ ናሙና በቁጥር ሲገለጽ ቁጥሩ እየጨመረ ወይም እየቀነሰ እንዲሄድ ተደርጎ በቅደም ተከተል መመዝገብና ቀመሩን ተግባርዊ በማድረግ ትክክለኛ የገበያ ዋጋው እንዲወጣ ይደረጋል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተሰበሰበው የአንድ ዕቃ፣ ንብረትና አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ በቅደም ተከተል የተቀመጠው ናሙና ብዛቱ ሙሉ ቁጥር ከሆነ መካከለኛ ዋጋ በሂሳብ ቀመሩ እንዲወጣ የሚደረግ ሲሆን የናሙናው ብዛት ጎዶሎ ከሆነ መካከል ላይ ያለው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ ሆኖ ይወሰዳል፣

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻጸም የስሌቱ ቀመር እንደሚከተለው ቀርቧል፤

ሀ) የተሰበሰበው የመረጃ ናሙና ዋጋ ብዛት ጎዶሎ (ኢተጋማሽ) ቁጥር ከሆነ ቀመሩ

$$\text{መካከለኛ ዋጋ} = \frac{(\text{ሀ}+1)^{\text{ኛ}}}{2} \qquad \text{ይሆናል፤}$$

ለ) የተሰበሰበው የመረጃ ናሙና ዋጋ ብዛት ሙሉ ቁጥር ከሆነ ቀመሩ

$$\text{መካከለኛ ዋጋ}= \frac{\left(\frac{\text{ሀ}}{2}\right)^{\text{ኛ}} + \left(\frac{\text{ሀ}}{2}+1\right)^{\text{ኛ}}}{2} \qquad \text{ይሆናል፤}$$

ሐ) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም

(1) "ሀ" የናሙናዎችን ብዛትን ያመለክታል፤

(2) "ኛ" ከትንሽ ወደ ትልቅ ከተደረደሩት ናሙናዎች ውስጥ ማዕከላዊ ዋጋው የሚገኝበትን ያመለክታል፤

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ በተቀመጠው መሰረት የወጣ የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በታክስ ባለሥልጣኑ የገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ይደራጃል፣

## 15. የገበያ ዋጋ መረጃ አጠቃቀም

1) የገበያ ዋጋ መረጃ ተጠቃሚ በታክስ ባለሥልጣኑ ተሰብስቦ የተደራጀውን የገበያ ዋጋ መረጃ ከታክስ ባለሥልጣኑ የገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ለታክስ ውሳኔ እንደመነሻ መጠቀም አለበት፡፡
2) ግብር ከፋዩ ያቀረበው የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ነጠላ ግብይት ዋጋ ከገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ያልተገኘ እንደሆነ የተመሣሣይ ወይም የተቀራራቢ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ መረጃ ተወስዶ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ የሚወስን ይሆናል፤
3) ግብር ከፋዩ ያቀረበው የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ነጠላ ግብይት ዋጋ ከገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ከሚገኘው ዋጋ ከአስር በመቶ በላይ ያነስ እንደሆነ ከገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ በሚገኘው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ የሚወስን ይሆናል፤
4) ታክስ የሚወስነው አካል ከገበያ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ ለሚፈለገው የእቃ፣ ንብረት አገልግሎት ወይም ጥቅም ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ በቀረበበት ጊዜ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳዩን የዋጋ መረጃ ካላገኘ ግብር ከፋዩ ካቀረበበት የሽያጭ ወራት ወደኋላ እስከ 6 ወር በመሄድ ለዕቃው፣ ንብረት አገልግሎት ወይም ጥቅም የተመዘገበን የገበያ ዋጋ መረጃ በመጠቀም ሊወስን ይችላል፣
5) በታክስ ባለሥልጣኑ ዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ የተደራጀው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ ለህዝብ ክፍት አይሆንም፡፡

## 16. የዋጋ አገማመት ጠቅላላ መርሆዎች ተፈጻሚነት

በዚህ መመሪያ በክፍል ሁለት እና ሶስት ድንጋጌዎች መሠረት የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የታክስ ባለሥልጣኑ በስፋት ተቀባይነት ያላቸውን የዋጋ አገማመት መርሆዎች በመጠቀም ትክክለኛ የገበያ ዋጋን የሚወስን ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# ተግባርና ኃላፊነት

## 17. የገበያ ዋጋ መረጃን የሚሰበስብና የሚያደራጅ ስራ ክፍል ኃላፊነት

የዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ዋጋ የሚሰበስብ፣ የሚያደራጅ፣ የሚተነትንና ለጥቅም ዝግጁ የሚያደርግ ስራ ክፍል፡-

1) ይህንን መመሪያ ተከትሎ የመስራት ኃላፊነት አለበት፣
2) በቅድሚያ የገበያ ዋጋ የሚሰበሰብላቸው የንግድ ዘርፎችን፣ ዝርዝር መግለጫቸውን፣ ብዛታቸውን፣ የሚሰበሰቡበትን የገበያ ቦታ፣ የመሰብሰቢያ ዘዴዎችንና ጊዜውን የመለየት ኃላፊነት አለበት፤
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተለይቶ የተሰበሰበውን የገበያ ዋጋ መረጃ በየዘርፉ የማደራጀትና ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ኃላፊነት አለበት፤

4) የተደራጀውን የገበያ ዋጋ መረጃ በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ ለሆነው ወይም በህግ መሰረት ይህን መረጃ የማገኘት መብት ለተሰጠው አካል ካልሆነ በስተቀር ሚስጥራዊነቱን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 18. የገበያ ዋጋ መረጃን የመስጠት ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት የገበያ ዋጋ መረጃ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ማንኛውም ሰው በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ትክክለኛ መረጃን በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 19. የገበያ ዋጋ መረጃ እንዲሰበሰብ የሚጠይቁ የሥራ ክፍሎች ኃላፊነት

1) በታክስ ባለሥልጣኑ ስር ከሚገኙ የስራ ክፍሎች ውስጥ ስጋትና ህግ ተገዥነት ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት፣ ታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ ታክስ ማጭበርበርና ምርመራ ዳይሬክቶሬት፣ በታክስ ባለሥልጣኑ ስር ያሉ ሌሎች የስራ ክፍሎች እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስጋት የሆኑና በገቢ አሰባሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጡትን የንግድ፣ አገልግሎትና የጥቅም ዘርፎችን በመለየት የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ለሚሰራው የታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የስራ ክፍል በወቅቱና በዝርዝር የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፤

2) የስጋትና ህግ ተገዥነት ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት በየጊዜው ታማኝ የሆኑትን ታክስ ከፋዮች በንግድ ዘርፋቸው፣ በንግድ ቦታቸው እና ውጤት ባስመዘገቡበት የግብር ዘመን በመለየት ለገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ ለሚሰራው የስራ ክፍል የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 20. የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ኃላፊነት

በታክስ ባለሥልጣኑ ውስጥ የሚገኘው የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል የገበያ ዋጋ መረጃን ለሚሰበስብ እና ለሚያደራጅ የሥራ ክፍል እና ለተጠቃሚ በሚያመች መልኩ የገበያ ዋጋ መረጃ የሚደራጅበት የገበያ ዋጋ መረጃ ቋት የማበልፀግ፣ አጠቃቀሙን የማሰልጠን እንዲሁም ማሻሻያ ሲያስፈልገው ማሻሻያ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

1/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በታክስ ህጉ መሰረት የተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ጥቅም ላይ መዋል የተጠበቀ ነው፡፡

## 22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገቢዎች ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ፤ 2017ዓ.ም**

***አይናለም ንጉሴ***

***የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር***